## 7. ምሥጢረ ክህነት

- ክህነት ማለት በቤተክርስቲያን ለእግዚአብሔር እና ለእግዚአብሔር ህዝብ (ለምእመናን) የሚሰጥ ልዩ መንፈሳዊ አገልግሎት ሲሆን፤ አገልጋዩ ካህን ሲበዛ ደግሞ ካህናት ይባላሉ።
- ክህነት የተጀመረው በብሉይ ኪዳን ቢሆንም ከአሥራ ሁለቱ የያዕቆብ ልጆች (ነገደ እስራኤል) አንዱ የሆነው የሌዊ ዘሮች ማለትም ሌዋውያን ብቻ ነበሩ ካህናት መሆን የሚችሉት።
- በሐዲስ ኪዳን ግን ክህነት የሚሰጠው በዘር ሐረግ ሳይሆን በመንፈስ ቅዱስ ጥሪ እና በቤተክርስቲያን ቀኖና መሠረት ነው። ይህም ማለት እውቀታቸውና ብቃታቸው የሚፈቅድላቸው (መሥፈርቱን የሚያሟሉ) ወንዶች ሁሉ ካህናት መሆን ይችላሉ (1ጴጥ 2፣5)።
- ዋጋ በመስጠት (ገንዘብ በመክፈል) ሥልጣነ ክህነትን መቀበል አይቻልም (ሐዋ 8፣18-26)።
- ክህነት አይደገምም ወይም አይታደስም፤ በድጋሚ ክህነት የሚቀበል ወይም የሚሰጥ ሁለቱም ከክህነታቸው ይሻራሉ (የሐዋርያት ቀኖና 68)።

የክህነት መዓርጋት (ደረጃዎች)

- በቤተክርስቲያን ሦስት የክህነት ደረጃዎች አሉ።




1ኛ ዲቁና፦

- ዲያቆን ከማግባቱ (ጋብቻ ከመፈጸሙ) በፊት በአንድ ጳጳስ በአንብሮተ እድ ይሾማል።
- ዋነኛ አገልግሎቱም የቄስ እና የጳጳስ ረዳትነት ነው (ሐዋ 6፣2-6)።
- በቤተክርስቲያናችን ከሙሉ የዲቁና መዐረግ በፊት ለተልእኮ የሚያበቁ መዓርጋት በቃለቡራኬ ይሰጣሉ።

2ኛ ቅስና፡-

- ዲያቆኑ ካገባ ወይም ከመነኮሰ በኋላ በአንድ ጳጳስ፣ በአንብሮተ እድ እና በንፍሐት (እፍ በማለት) ቅስና ይሾማል፡፡
- አገልግሎቱም ሥልጣነ ክህነት ከመስጠት፣ ሜሮን ከማዘጋጀት፣ አዲስ ሕንፃ ቤተክርስቲያን፣ ጽላት፣ መንበር… ከመባረክ በቀር ጳጳሳት (ኤጲስቆጶሳት) የሚፈጽሙትን ማንኛውንም የክህነት አገልግሎት መፈጸም ነው፡፡
- ህግ ገብቶ (ጋብቻ ፈጽሞ) ቅስና የተቀበለ ካህን በክህነት ማገልገል የሚችለው በትዳሩ እስከተወሰነ ድረስ ብቻ ነው፡፡ የትዳር አጋሩ በሞት ወይም በሌላ ምክንያት ብትለየው ሥርዓተ ምንኩስና ፈጽሞ ሥልጣነ-ክህነቱን መጠበቅ/ ማጽናት ይችላል፡፡

3ኛ ጵጵስና፡-

- አንድ ዲያቆን በድንግልና መንኵሶ ቅስናን ከተቀበለ (ካህን ከሆነ) በኋላ ተመርጦ በመላ የሲኖዶስ አባላት ወይም በሁለትና ከዚያም በላይ በሆኑ ጳጳሳት ጵጵስና (ኤጲስቆጶስነት) ሊሾም ይችላል፡፡
- አገልግሎቱም ምሥጢራትን ከመፈጸም ጋር ጠቅላላ የቤተክርስቲያን መሪነት እና ጠባቂነት ነው (ሐዋ 20፣28)፡፡

ክህነት ለመቀበል የሚያስችሉ አጠቃላይ መስፈርቶች

- በሦስቱም መዓርጋት የሚሾሙት ዲያቆናት እና ካህናት ሃይማኖታቸውን በሚገባ የሚያውቁ (የተማሩ)፣በምግባር የታነጹ፣ በጠባያቸው የተመሰገኑ እና የእግዚአብሄርን ቤተክርስተቲያን በተገቢው መንገድ ሊያስተዳድሩ የሚችሉ መሆን አለባቸው፡፡
- ዲያቆናት፡- ሐዋ 6፣3፤ 1ጢሞ 3፣8-13፤ ፊሊጵ 1፣1…
- ካህናት (ቀሳውስት እና ጳጳሳት/ኤጲስቆጶሳት)፡- ሐዋ 20፣28፤ 1ጢሞ 3፣1-7፤ ቲቶ 1፣6-8፤ ቲቶ 2፣1-2፤ ፊሊጵ 1፣1…

ክርስቲያኖች ሁሉ ሥልጣነ ክህነት አላቸውን?

- አንዳንዶች ‹‹በምእመናን መካከል ምንም ልዩነት የለም፤ ሁላችንም አገልጋዮች (ካህናት) ነን›› ይላሉ፡፡ ነገር ግን ከሥልጣነ ክህነት ጋር በተያያዘ ይህ አባባል ስህተት ነው፡-
    - ካህናት የሚሾሙት ተመርጠው ነው፤ ቁጥራቸውም የተወሰነ ነው (ሉቃ 6፣12-13፤ 1ጢሞ 3፣13፤ ሐዋ 20፣28-14፣23፤ ኤፌ 4፣11)፡፡

- ለሌላ ያልተሰጠ ልዩ ሥልጣን ማለትም የመፍታትና የማሠር (ኃጢአትን የማስተስረይ) እና ምእመናንን የመጠበቅ ሥልጣን ተሰጥቷቸዋል (ማቴ18፣18፤ ዮሐ 20፣21-23)፡፡
- ሐዋርያት በሲኖዶስ (በጉባዔ) በይሁዳ ምትክ ማትያስን መምረጣቸው ክህነት ከሌላው ህዝባዊ አገልግሎት የተለየ መሆኑን ያሳያል (ሐዋ 1፣15-26)፡፡
- ክህነትም በሐዋርያት ብቻ ያበቃ ሳይሆን እስከዓለም ፍጻሜ ድረስ ለተከታዮቻቸው ሁሉ የተሰጠ ነው (ማቴ 28፣20)፡፡